# የተበረዘ መንፈስን ማዳን

በቅርቡ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌና በ አቶ በውነቱ ዘለቀ የወጣውን ጽሁፍ በመመርኮዝ ከተለያዩ ወገኖች በወቅቱ የትግል አቅጣጫ ላይ የተሰነዘረውን አስተያየት አንብቤ ለጸሃፊዎቹ ያለኝን አክብሮት በውስጤ ከመግለጽ ባሻገር እነዚህ ወገኖች ለሃገራችን ህዝብ ለወደፊት ይበጃል ያሉትን አቅጣጫ በእነሱ እይታ የታዩትን ዝርዝር ነጥቦች ለመዳሰስ እሞክራለሁ:: ከሁሉም በላይ የሚታገሉለት ህብረተሰብ ሃሳባቸውን በትክክል እንዲጨብጥ በሃገራችን ቋንቋ በሆነው አማርኛ ማስፈራቸው ዛሬ አንዳንዶች የአማርኛው ፊደል ቴክኖሎጂ ባለመስፋፋቱ ተቸግረው አልያም በሚገባቸው በእንግሊዝኛ ለመጻፍ ለተገደዱ ወገኖች ትምህርት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ:: ብዙ ወንድሞቻችን እና አልፎ አልፎም ትንሽ ቁጥር ያላቸው እህቶች በእንግሊዝኛ የሚያስተላልፉትን መልእክት ምን ያህሉ የሀገራችን ህዝብ እንደሚረዳው ሳስብ ስለሚጨንቀኝ ነው::

በተለይ እንደኛ ደሀና ኋላ ቀር የሀሳብ ማስፋፊያ መንገዱም ጠባብ በሆነ ህብረተሰብ ውስጥ የህብረተሰቡን አስተሳሰብ ሊለውጥ የሚችሉ ገንቢ ሀሳቦች ተገቢ ሚናቸውን ስለመወጣታቸው ማሰቡ ተገቢ ነው:: እነ አቶ አንዳርጋቸው ያቀረቡት ሀሳብ ተግባራዊነቱ በጥቂቶች ሳይሆን በህብረተሰቡ ነው; በዚህ አጋጣሚ ለሀገራችን የታገሉ ሁሉ ከትችትና ከወቀሳ የዳኑ ባለመኖራቸው እነ አቶ አንዳርጋቸውም ሆኑ ሌሎችን አደራ የምለው አስተያየቴ ማንነታቸውን ለመዳፈር ሳይሆን የሀገራችን ጉዳይ የጋራችን ነው እና አንዳንዴ ባንግባባ በተግባባነው ልንጓዝ የምንችል መሆኑን በትህትና እያሳሰብኩ ነው::

በመጀመሪያ የጽሁፉ ዋንኛ ትኩረት ያለፈውን በመገምገም መጪውን የሀገራችን ሁኔታ ለመለወጥ ምን መደረግ ይኖርበታል የሚል ከተቆርቋሪነት የመነጨ ስሜት ነው:: ጽሁፉ ግለሰባዊ ወይንም ቡድናዊ ሳይሆን አንድ የፖለቲካ ድርጅት ቀጥተኛ አመራር ወይም መግለጫ የሚመስል አቀራረብ ያለው ነው:: ምናልባት አቶ አንዳርጋቸው በቀድሞ መጽሃፋቸውና በቅርቡም ባወጧቸው ጽሁፎች እንድሁም በቅንጂት የአመራር አባልነታቸው የማቃቸው ቢሆንም ይህ በማኔፌስቶ መልክ የቀረበውን የወደፊት የሃገራችንን የትግል አቅጣጫና መፍትሄ የሚያመላክት ጽሁፍ ይዘቱን ለመረዳት ብዙ አያስቸግርም:: የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ከሞላ ጎደል አለም አቀፍ የሃይል ሚዛን አሰላለፍ እና አቅጣጫ የዳሰሰ ለመሆኑ አያጠያይቅም::ጥያቄው ግምገማውና መደረግ ያለበት መገጣጠሙን ማረጋገጥ ነው

## ያለፈውን በትክክል መገምገም ለወደፊቱ መፍትሄ ግማሽ መንገድ መሄድ ነው፤

አንድን ታሪካዊ ወይም ነባራዊ ሁኔታ ለመገምገም የሚያስችሉ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችና የመነሻ ሃሳቦች መኖር እንዳለባቸው ግልጽ ነው:: እንደ ፖለቲከኛ ወይም ለፖለቲካ ስልጣን የሚታገል ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚታገለውን ክፍል ለመታገያ የሚጠቀምበት የመገምገሚያ እይታው የሚያተኩረው በተቃራኒው ደካማ ጎን ማለትም በእርሱ አመለካከት የህዝብን ድጋፍ ያስገኙልኛል በሚላቸው የኢኮኖሚ የፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሆኑ ይታወቃል;; ተቃዋሚዎችም ሆኑ ስልጣን ላይ ያለው አንዱ ከሌላውየተሻለ መሆኑን ከተቻለ በሰላማዊ መንገድ ካልተቻለም በኀይል ማረጋገጥ ይፈልጋል:; አንዱ ሌላውን ለማጥቃት በህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ከማጋለጥ አልፎ ለፖለቲካው አላማ ያሳካልኛል ብሎ ከገመተ የልዩነት ቀዳዳዎችን ሁሉ እንደሚጎረጉር አንኳንስ በእንደኛ አይነቱ የመቻቻል ፖለቲካ ባልዳበረበት ይቅርና የዳበረ ፖለቲካ አላቸው በሚባሉት ህዝቦች የሚታይ ህብረተሰብም እስካለ ድረስ የሚቀጥል እውነታ ነው::

በርካታ የሃገራችን ፖለቲከኞች የትግል ስልታቸው ተቃዋሚነት የሚቃወሙትን እስከ መጨረሻ መጥላት በሚለው የጥላቻ ፓለቲካ ሲደጋገም ነው የምናየው:: ወያኔ ኢህአዴግ ባለፉት 17 አመታት በኢትዮጵያ መንግስትነት የፈፅመውን ጥፋት ወይም በደል ለመፈጸም የተጠቀመበት ያለፈውን ስርአት ሙሉ በሙሉ በመርገም ስነልቡናዊ ጦርነት ነው;; በተለይም የብሔር ብሔረሰብን ጥያቄ እንደዋነኛው የስልጣን አውታር በመጠቀም ለችግር ሁሉ ምክንያቱ ያለፈው ስርአት እነደነበረና ያም ስርዐት ለአንድ ብሄረሰብ የቆመ በማስመሰል ወገን ከወገኑ እንዲባላ የከፋፍለህ ግዛ ፕሮፓጋንዳ በህዝቡ ውስጥ በማሰራጨት ለተወሰነ ጊዜ ተቀባይነትን ያገኘ መስሎ ቢታየውም ስልጣኑን ካረጋጋ በኋላ ያንኑ ጥያቄ እሱ እንደሚፈልገው አንጂ ሌሎች እንደሚሹት ሊመልስ ባለመቻሉ በየአቅጣጫው አመጽ ታይቷል;;

በስልጣኑ አፍላ ደርግን ብሎም ኢሠፓን ጠረኛ ሲል ቆይቶ ደርግ የተዋጋውን ጦርነት ሁሉ ተዋግቷል እየተዋጋም

ነው:: እንዲያውም የጦርነት ጥሩና መጥፎ ባይኖረውም ሁለቱም በስልጣን ላይ እያሉ ያደረጉትን ጦርነቶች በመመርመር ሀገራዊ ጦርነት የቱ እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም::

ደርግን በሰፈራ ህዝቡን ማፈናቀሉን በኮነነው ማግስት በአፈጻጸም ልዩነት ቢኖርም በራሱ የአፈጻጸም ስልት ሲተገብረው ታይቷል:; ከሁሉም በላይ ደርግን የኮነነበት የዘር እልቂትና ጸረ ዲሞክራሲነትን በእራሱ የቀድሞ አባላት የተመሰከረውን ‹‹እስር ቤቱ አንድ ብሄረሰብ ይሸታል›› የሚያሰኘውን ተግባር ፈጽሞአል:: እየፈጸመም ነው::በተወሰነ ብሄር ላይ ሌሎች ብሄረሰቦች እንዲነሱ የጥላቻ መርዝ ረጭተል;; ከየዘሩ ብዙ ትምክህተኞች ብዙ ጠባቦች እንዲፈጠሩ ረድቷል::

ደርግን በሙስና የተዘፈቀ መንግስት ነው ብሎ ሲኮንን እንዳልነበረ በደርግ ዘመን አብዛኛውን ህዝብ ሚሊዩንን የሚያውቀው በሰው ስም መጥሪያነት አልያም በሃገር ወይም በክፍለ ሃገር በጀት እንዳልነበረ ዛሬ አንድ ግለሰብ ሳይሆን ብዙ የሙስና ሚሊየነሮችን ፈጥሮአል::

ደርግ በለየለት የሶሻሊስት ርእዩተአለም እየተመራ የግል ንብረትና ሃብትን በመንግስት ስር ማድረጉን እንዳላወገዝልን ኢህአዴግ በቅይጥ ኢኮኖሚ ስም የሀገሪቷን ዋና ዋና ኢንቨስትመንት ተቋሞች ኩባንያዎች የንግድና የአገልግሎት ተቋሞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በድርጅት ባለቤትነትና ይዞታ እየመራ ነው::

በአጠቃላይም ደርግ አምባገነናዊ መንግስት የወታደር መንግስት ፋሽስት መንግስት ያልተባለው አልነበረም:: የደርግን ወታደራዊነት በዘረኛ መንግስትነት ካለመቀየሩ በስተቀር ኢህአዴግ ደርግን ሲል የነበረውን ሁሉ እሱም ተብሎዋል:; የማእረግ ልዩነትና ቁመናም ካልሆነ በቀር ኮሎኔል መንግስቱና እና አቶ መለስ መካከል ያለው ልዩነት አንዱ አቶ ሌላው ኮሎኔል መሆናቸው ተነግሮአል ;; የአመራራቸውን ዲሞክራሲያዊት በምክር ቤት ስብሰባ ወይም በቴሌቭዥን የምናውቀው ነው:: ታዲያ ዛሬ የኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን ስንቃወም ስልጣን ብንይዝ ያልነውንና የተቃወምነውን ላለመፈጸም የሚያስችል ድርጅታዊ ስነልቦናዊ ዝግጅታችን በመነፈስም ይሁን በተጨባጭ ሁኔታ ያልነውን ላለመሆናችን ማረጋገጫ ይኖር ይሆን ? ባለፉት የትግል አመታት በየአቅጣጫው ብቅ ብቅ ያሉት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ገና ስልጣን ሳይዙ በትግሉ ሂደት ያወገዙት ወይም ሲቃወሙ የነበረውን አልፈጸሙት ይሆን ?

በመሰረቱ የኢህአዴግ መንግስት ከጊዜ ወደ ጊዜ በዲሞክራሲ በፍትህና በእኩልነት ስም እየማለ የሚፈጽመውን ያገጠጠ ጸረ ዲሞክራሲ አካሄድ ለማስለወጥ መደረግ ያለበት ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑ ባያጠያይቅም በዚህ ወቅት የህቡእ ትግል ጥያቄ መነሳቱ የፖለቲካ ስልጣን በየትኛውም መንገድ መምጣት አለበት ወደሚለው የተለመደ ሽክርክሪት ታሪካችን የሚመልሰን ሃሳብ ነው:ብዬ እገምታለሁ ;;

የህቡእ ትግል ወደ ትጥቅ ትግል ማደጉ የማይቀር በመሆኑ

1/በተለይ ጎሳን መሰረት ባደረገ የፖለቲካና ኢኮኖሚ አደረጃጀት ይህ ስልት ወዴት ሊወስድ እንደሚችል በቂ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል ;;

2/የህቡእ ትግል ቢጀመር ከተቃዋሚው ይልቅ ኢህአዴግ ካለው የሰለላ መረብ ስፋትና ልምድ አንፃር የሚፈነድቅበት ሁኔታ ከመፍጠር ባሸገር ዳግም የሀገሪቱን ምርጥ ልጆች በዚህም ሆነ በዚያኛው የተሰለፉትን ለእልቂት መዳረግ ነው;;

3/አለም አቀፍ ሁኔታው በጸረ ሽብርተኝነት ስም በኢህአዴግ መንግስትና በተለይም በአሜሪካ መንግስት መካከል የተፈጠረው የጠበቀ ግኑኝነት ለህቡእ ትግል ትርጉም ትክክለኛ ግንዛቤ ሊያስገኝ አይችልም

ዛሬ በትጥቅ ትግሉ እየተሳተፉ ከሚገኙት ድርጅቶች ዋናዋናዎቹ አካባ ኦጋዴን ነጻ አውጭ ግምባር አርበኞች ግምባር ወ.ዘ.ተ በሻቢያ አስተባባሪነት በትጥቅ ትግሉ ኢህአዴግን ቢያስወግዱ ሀገራችን ቀን ይወጣለታል ብለው የሚገምቱ ቢኖሩ መገመት መብታቸው ቢሆንም ለኢትዮጵያ ስለማሰባቸው ግን ደጋግመው ሊጠይቁ ይገባል::

# የቅንጅት ሰላማዊ ትግል ጉዞ

ቅንጅት የወያኔን የፖለቲካ መስመር በማጋለጥ በአገርና አለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን አግኝቶ አገርና ህዝብን ለማስተዳደር የእራሱንም ውስጠ ህይወት ያሳድጋል በሚል እምነት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ተስፋ ተጥሎበት አብዛኛው ህዝብ አደባባይ ወጥቶ የራሴ ድርጅት ነው የሚለውን የመረጠበት እና የተለያዩ ፓርቲዎችንም ቅን አመለካከት ያገኘ ድርጅት ነበር::

ስልጣን ቢይዝ ኖሮ የሚኖረውን ስዕል ከወዲሁ ለመጠቆም ቢያስቸግርም በጊዜው ቅንጅት የህዝብ ቤት ሆኖ ታይቷል:: ዳሩ ግን ብዙም ሳይገዝ በራሱ አመራር ውስጥ በተፈጠረው የስልጣን ሽኩቻም ሆነ የአፈጻጸም ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ ለማስታረቅ አለመቻላቸው የታገሉለትን አላማ መልሰው ሲታገሉት አየን:: ደጋፊዎቻቸውና ቅንጅትን አምነው በመንግስት ላይ የማዕቀብ ዘመቻ ያስተላለፉትን መንግስታት ሁሉ እጅግ አስደነገጡ አሳዘኑ ;; ልዩነትን አቻችሎ ከሁሉም በላይ የህብረትና የአንድነቱን ጥያቄ ጎልቶ በሚያስፈልግበት ወቅት ከወያኔ ባላነሰ አንዱ ቡድን ሌላውን ሲያወግዘውና የድርጅቱን ውስጠ ህይወት ሲያዘረከርኩት ሰማን::

የሚታገሉለት አገርና ህዝብ ተዘንግቶ የአንድ እናት ልጆች ፍልሚያ በዙፋን ዙሪያ ሆነ:: አንዳንድ ግለሰቦችና የፅሁፍ ሰዎችም የቅንጅት ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊነት ተዘንግቶ አንደበትና ብዕራቸው የግለሰብ ማሞካሻና ማሞረጃ ሆነ ስለህዝባዊ መንግስት አመሰራረት ስለኢትዩጵያ ህዝቦች አንድነት እየተነገረ የትግሉ አቅጣጫ ተቀይሮ በብሄረሰብ በጓደኛነት በቤተሰብ መደራጀት ታየ; ይህ ሃላፊነት የጎደለው የንትርክና የወሬ ጊዜ የሚኮራበት ታሪኩን የሚያወርስ ለተተኪው ትውልድ ት/ቤት የሚሆን መሪ ከማሳጣት በቀር ያስገኘው ውጤት አለመኖሩን ነው::

ቅንጅት ለህዝባዊ ድል በሙሉ አመኔታና ውክልናን አግኝቶ ለስልጣን የበቃ ፓርቲ ነበር:: ሆኖም በገዥው መንግስት ጉልበተኝነት በራሱ በድርጅቱ አፈጻጸም ችግር ህዝባዊ ድልን ቢጨበጥም ይህ አካሄድ ያስተማረን ሆነ የጠቆመን ስልት ጭራሽ <u>ህዝባዊ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ ሊገኝ አለመቻሉን አልነበረም;;</u>

**እልህና ቂመኝነት የትም እንዳላደረሱን እያየነው ነው::** አለም ከደረሰበት የጦር መሳሪያ ቴክኖሎጂ ደረጃ ጠመንጃውም ፈንጂውም የሚያጠፋው የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም እየሆነ መጥቷል:: በሰሜን በደቡብ በሁሉም መአዘናት ለጦርነት የተዘጋጀ ሰራዊት ከትሞአል:: ጎረቤቶቻችን በራሳቸውም ሆነ በውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት እየተተራመሱ ናቸው:: የምስራቅ አፍሪካ አጠቃላይ ፓለቲካ እየተቀየረ ነው;; ትጥቅ ትግል ያስፈልጋል ቢባል እንኳን ለትጥቅ ትግል የሚያመች የኤርትራ መንግስት ብቻ ነው:: ይህም ማለትም በምንም መልኩ ከኢህአዴግ ሻቢያ ለኢትዩጵያ የሚያስብ መንግስት ነው በእርሱም ድጋፍ መላ ሀገሪቱን ወይም አንድን ክፍል ከኢህአዴግ በጦርነት ነጻ አወጣለሁ የሚል ቡድን ወይም ድርጅት ፍላጎቱ ለኢትዩጵያ ዘለቄታ ሰላም ሳይሆን የሚያተርፍላት ሰቆቃ እና ችግርን ነው:: የኮሚኒስቶቹ አመለካከት የሆነው የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ሁልጊዜ አይሰራም ጠላት ጠላት ነው:: የጠላትነት ጊዜውን ነው የምንቀይረው በመሰረቱ አንድ ህዝብ ለሌላው ጠላት የሚሆንበት መሰረት የለም የአበዱ መሪዎች ግን ሕዝብን ከህዝብ በጠላትነት ያፋጁታል::

በመሆኑም ከኢሳያስ መንግስት ጋር ሆኖ የገዛ ህዝቡን የሚወጋ ለኢትዮጲያ ህዝብ ወዳጅነቱ አጠያያቂ ነው:: ለታክቲክ በር ለማግኘት ወዘተ የፖለቲካ ቁማር ነው:: እዚህ ላይ ለዚህ ሁሉ ችግር የእህአዴግን ተጠያቂነት ለማድበስበስ አይደለም:: ሀቁ ግን ከጥቂት ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ደንታ ከሌላቸው አመራር አባላት በስተቀር ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊ ድርጅትና መንግስት መሆንኑ ጥያቄ ውስጥ ካለማስገባቱ ነው:: ለሀገሪቱ የተሳሳተ የፖሊሲ አመራር የሚሰጥ የፓለቲካ ድርጅት መሆኑ ነው::ፖሊሲው ደግሞ በአብዛኛው አባላቱ ዘንድ ድጋፍ ያለውና የተወሰነ ህብረተሰብንም ክፍልም የሚያቅፍ ከሆነ መፍትሄሔው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ትግሉን ማጠናከር ነው::

ስለዚህ ለዲሞክራሲው እድገት መመዘኛችን ያለፈውን ምርጫ ብቻ አድርገን ከወሰድነው በቂ ግንዛቤ ስለመገኘቱ ያጠራጥራል:: በስልጣን ላይ ያለን አንድ አምባገነን መንግስት ከአምባገነን ጉዞው አርቆ እና የባሰ መከራ በህዝብ ላይ

እንዳያመጣ አግዶ ማቆየቱ ራሱ የዲሞክራሲው ትግል አካል እና ድል ነው:: መልሰ ብሎ ማስታወስ ሚገባው እንደ ኢህአዴግ የጎሳ ፖለቲካ አጀማመር ቢሆን ኖሮ ዛሬ ምንታገልላት አገር እና ህዝብም ባልኖረም ነበር::በሂደት ግን እሱም እየተለበለበበት ሲመጣ በግልጽ ሊታገለው ባይሞክርም በተለያዩ ግዜያት በፌዴራል አስተዳደር ላይ ያስከተላቸውን ማሻሻያ መሰል እርምጃዎች ማጤን ተገቢ ነው::

**ከኢህአዴግ ባለነሰ ተቃዋሚዎች ተጠያቂዎች ናቸው::** ለምን? ከወቅቱ ጋር የማይሄድ ፓለቲካና የፖለቲካ ፕሮግራም ይዘው መንቀሳቀሳቸው ነው:: እዚህ ላይ በግልጽ መነሳት ያለበት ሁኔታ መሰረታዊ የሀገሪቱ ችግሮችን ያልገመገመ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውጤቱ ለራሱም ሆነ ለሀገሪቱ የማይበጅ መሆኑን ነው:: በሀገሪቱ አሁን ያሉትንና የነበሩትን የፖለቲካ ድርጅቶች በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል::

1. በብሔር ብሔረሰብ ስም የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ከነዚህ ዋናዋናዎቹ ኢህአዴግን ኦነግን አብኮን ደቡብ ሕዝቦችን የመሳሰሉትን ከ 1970 ዎቹ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና ከዚያም ወዲህ የተፈለፈሉትን ያጠቃልላል።

2. በሕብረብሄርነት የተደራጁ እንደ እነ ኢህአፓ መኢሶን ኢሠፓ ኢዴፓ ቅንጅት ወዘተ ያጠቃልላል።

እንግዲህ ጥያቄው በአንድ የተወሰነ ወቅት የሚመሰረት የፖለቲካ ድርጅት ሲመሰረት ለትግሉ የሚያመላክታቸው ችግሮችን ማጤን ለመፍትሄው ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲያገኝ ይረዱታል:: አንዱ ጥያቄው የብሔር ጥያቄ ወይም የብሔርን ችግር ዋናው አድርጎ ሌላው በህበረብሄርነት ከተንቀሳቀሰ በምንም መልኩ የተጠነናከረነና የህበረት ትግል ማድረግ አይቻልም። ለምሳሌ ህብረትን ከመጀመረያ ጀምሮ የሚያንገዳግደው ይሄው ችግር ነው;; የሁለቱን ትግል የማቀናጀት ጥያቄ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መፍትሄ ሊሰጡት የሚገባ ቁልፍ ጉዳይ ነው:: ኦነግ ከ 40 አመት በላይ የታገለ ድርጅት መሆኑ ይታወቃል:: በ40 አመት ውስጥ ጥያቂው ወይም የተነሳበት አላማ ካልተመለሰ ለምን አልተመለሰም የሚለውን መመርመር ይኖርበታል:: ዛሬም ሕብረ ብሄር ድርጅቶች በኦነግ ላይ ጥርጣሬ አላቸው ለምን ቢባል ኦነግ ዛሬም የሚንቀሳቀሰው የኦሮሞ ህዝብን ነጻ ስለማውጣት አልያም ደበስበስ ባለ መልኩ የህዝቦችን እድል በራስ መወሰን በሚለው የትግል መስመሩ ነው:: ኦነግ አልፎ አልፎ በሚያወጣቸው መግለጫዎቹ ስለ ኦሮሚያ እንጂ ስለ ኢትዮጵያ ብዙም ደፍሮ ሲናገር አይታይም:: ምናልባት ድርጅቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሀይሎች ጋር በድፍረት የጋራ አቋም ለመያዝ የተገደደበት ሁኔታ ቅንጅት ከተመሰረተ በኋላ ነው:: በወቅቱ በቅንጅትም ሆነ በእራሱ በኦነግ ደጋፊዎች መካከል የተፈጠረውን የሁለት መከፈል አዝማሚያ በራሳችው ድርጅቶች ህልውናም ላይ ያስከተልውን ተጽኖ አይተናል:: ኦነግን በሌላው ዘንድ ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ ያደረገው የትግል ስልቱ አይደልም የትግሉ መሰረታዊ አላማ ነው:: ኦነግ እንደሌሎቹ የፖለቲካ ሃይሎች የመገንጠል ጥያቄ ያነሳበት ወቅት አለም አቀፍ ሁኔታዎችም ያግዙት የነበረበት ወቅት ነው:: የ60ዎቹን ጭንቅላት ከ 2000 ጋር ማስታረቅ ብሎም ለዚህ የሚያመች ፖለቲካ አደረጃጀት እና የትግል ስልት መንደፍ የሚጠበቅበት ቢሆንም የጎሳ ፖለቲካ ስሜቱ ከኢህአዴግ መሰረታዊ የፖለቲካ አነሳስ ጋር አንድ ስለሚያደርገው ከሌሎች ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ ወይም እራስን የማየት ድፍረት የተመላበት እንቅስቃሴ ሲያደርግ አልታየም:: ይህ ማለት ግን የኦሮሞ ሕዝብ እንደሌላው ሕዝብ ለደረሰበት የእድገት ደረጃ አስተዋጾ አላበረከትም ማለት አይደለም::

አንድ ጨቋኝ ብሄር በሌለበት የተውሰነ ብሄርን ብቻ ሙብትና ጥቅም ለማስከበር የሚደረግ ትግል በሌላው ላይ የበላይ ለመሆን የሚደረግ የዲሞክራሲ የፍትህ እና የእኩልነት ጥያቄን አደጋ ውስጥ የሚከት ነው። እዚህ ላይ ባለፉት ጨቋኝ ስርአቶች እና አሁንም ባለው የኢህአዴግ አስተዳደር ምክንያት ህዝቦች በሚያመቻቸው መልኩ ተደራጅተው ለእኩልነትና ለነጻነት የሚያደርጉትን ትግል ለማንኳሰሳ አይደለም ወይም በኅብረብሄርነት ተደራጅተናል እንደሚሉት አንዳንድ ድርጅቶች የነበረን ወይም ያለን ጭቆናና መረገጥ እንዳልነበረ አድርገው በመመልከት ምናልባትም እነሱ የሚፈልጉዋት ኢትዮጵያ የአንድ ብሄረሰብ ቋንቋ ባህል አመራር የሰፈነበት ስርአት የሚናፍቁትን "ኅብረብሄርተኝነት" ስሜት ለማንፀባረቅም አይደለም::

የብሄር ብሄረሰብ ጭቆና እንደነበረ አምነው የተጨቆነው ብሄረሰብ ጥያቄ የጋራ ጥያቄ በመሆኑ በመልካምና ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር አለም ከደረሰበት የእድገት ደረጃና ከኛ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር መመለስ አለበት ብለው እምነት ይዘው በተነሱ ድርጅቶችና ጥያቄው ወይም ጭቆና ያልነበረ መነሳትም የሌለበት በደፈናው አንዲት ኢትዮጵያ ማለት አለብን በሚሉ ክፍሎች መካከል አሁንም ጥርጣሬ መኖሩ የችግሩ ምንጭ ነው:: ይህን አምነን በጋራ ወደፊት ሁኔታው እንዳይደገም የሚስችል ስርአት እንፍጠር ብሎ የሚታገልን ክፍል ከሌላው ጋር እያደበላለቁ የብሄርን ስም ብቻ በማንሳቱ በተጠርጣሪነት አለም ውስጥ እንዲገባና ተቃዋሚውን ሃይል የኢህአዴግ ሰላባ አድርጎታል

ስለዚህም በብሄር ስም የተደራጁ ድርጅቶችም ሆኑ በኅብረብሄርነት የተደራጁት ከወቅቱ አገራዊ እና አለምአቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የብሄር ብሄረሰብን ችግር ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሊፈታ የሚያስችል መተማመን እና መብሰልን የሚጠይቅ መፍትሄ ይዘው ሊቀርቡ ይገባል:: በሌላ በኩል በህዝቦች መካከል መጠራጠርንና የቂም በቀልን መፍትሄ ለይቶ መገንዘቡ ወቅቱ የሚጠይቀው ነው

በኢትዮጲያችን ከ50 እና 60 አመት በላይ የታየውን የትጥቅ ትግል ውጤትና የ5 አመት ሰላማዊ ትግል ውጤት በሚገባ ለመረመረው ሰላማዊ ትግሉ እያሳየ ያለው ውጤት የላቀ ነው:: ስልጣን ካልያዙ አልታገልም ካልተባለ በስተቀር ሰላማዊ ትግል የገፉት ድርጅቶች በትጥቅ ትግል ከተሳተፉት የበለጠ ሕዝባዊ መሰረት ጥለዋል: እየጣሉም ናቸው:: ኢህአዴግ ሳይወድ በግድ ኢትዮጲያዊ ቀለም እንዲቀባ አድርገውታል;; ቀለሙ ቢፋቅ በራሳቸው ቋንቋ ምን እንደሚመስል አቶ መለስ ቢያውቁትም በግልጽ በሌላ ቀለም መታየቱ አንድን አካባቢ ብቻ ሳይሆን መላውን ኢትዮጲያ የሚያስቆጣ መሆኑን እየተረዱት መጥተዋል:: ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ለስልጣን ያለመብቃት ችግር የኢህአዴግ አምባገነናዊ መሆን ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚዎቹም ድርጅታዊ ጥንካሬ: አንድነት የሁሉም ኢትዮጲያ ድርጅት የመሆን ብቃት ማነስ ነው:: በድርጅቶች መካከል መከባበር እና መቻቻል ልዩነቶች በውይይት ለማጥበብ አለመሻት ነው:: አንዳንዶቹ ለረዥም አመታት ሲታገሉለት የነበረውን የሰላማዊ ትግል ዛሬ እነርሱ የፈጠሩት ይመስል አዲስ ራእይ ይዘን ቀረብን ብለው ሲፎክሩበት ነው::አልያም የአዲሶቹ አነሳስ የቀድሞዎቹን በሕዝብ ዘንድ ያለ ተቀባይነት ያደበዝዝብናል ብለው የሚፈሩ ግለሰቦች ሲያፈነግጡ ነው:: ግለኝነት ትላንትም ዛሬም የእኔ ማለት በሽታ የስነልቦና በሽታ ነው::

እዚህ ላይ ትልቁ ጥያቄ በትጥቅ ትግል መወገድ ያለበት መንግስትም ቢሆን የሰላማዊ ትግል ጥያቄ ቦታ የለውም ማለት አይደለም:: መወገድ የለበትም ነገር ግን የለውጡ አካል ሊሆን የሚችል መንግስት ከሆነ ለመለወጥ ምን እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባሉ ? ሰላማዊ ትግሉ በምን መልኩ መጠናከር አለበት የሚለው የትኩረት አቅጣጫና የሚያወያይ ይሆናል::

በበኩሌ ኢህአዴግን የማስወገድ ፖለቲካ ቦታ ያለው አይመስለኝም ኢህአዴግን አስገድዶ ለሕዝብ ሁሳኔ ተገዥ በማድረግ በሰላማዊ መንገድ ስልጣን እንዲያዝ ወይም ስልጣን እንዲለቅ ማድረግ ይቻላል የሚል ተስፋ አለኝ:: ለዚህ አይነቱ ትግል በድፈፍረት እና በግልጽ ሲታገሉለት የነበረ አላማ በመሆኑ ይኸው ሊቀጥል እንደሚገባ አምናለሁ:: ዳሩ ግን በሰላማዊ ትግሉ የመስዕዋትነቱ ገፈታ ቀማሽ የድርጅት መሪዎች ጥንካሬ ቁርጥኛነት ይወስነዋል:: ሰላማዊ ትግል በሀገር ውስጥ ሆኖ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ሁሉ እየከፈሉ እስር ግርፋት ሞት ጭምር እየተቀበሉ የሚታገሉበት የትግል ስልት ነው:: ልንማር የሚገባው ትልቁ ቁም ነገር ግን ከባሕር ማዶ ሆኖ ኢትዮጲያን ህዝብ ትግል ለመምራት የሚደረገውን ግርግር አቁሞ የትግሉ ባለቤት ለሆነው ህዝብ ሰላማዊ ትግሉን እንዲያጠናክር አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው:: እነዚህ ሁኔታዎች ምንድናቸው ?

**1ኛ. በምንም መልኩ በእንዲህ አይነቱ የተበታተነ ሁኔታ ይህችን አገር ዲሞክራሲያዊ አመራር ለማስጨበጥ አይቻልም::** በብሔርም ሆነ በህብረብሔር የተደራጁ ድርጅቶች ፕሮግራማቸውን መርምረው አቋማቸውን አስተካክለው ወደ ተጠናከረ ሕብረት መምጣት ይገባቸዋል:: ለዚህም በቅንጅትን ሆነ በህብረት የተሰባሰቡት ከግል ዝናና ፍላጎት ተላቀው (ዋነኛው ችገር እሱ ስለነበር) የፖለቲካ አስተሳሰብ መለያየት ሊኖር ቢችልም አብሮ መስራትም እንደሚቻል ለሕዝብ ሲያስተምሩና የሰላማዊ ትግልን ከራስ ሲጀምሩ ብቻ ነው: በሀቅ ለሀገሬ ቆሚያለሁ የሚል ድርጅት እንደሱ ለሀገሩ የቆመ ድርጂት ነው ብሎ ከሚያምነው ጋር ህብረት ለመፍጠር የማያስችለው ሌላ ምንም ሳይሆን ራስ ወዳድነት

ነው;;እንግዲያውስ እስካሁን ካየነው በትግል ፕሮግራሙና ብቃት አንዱ ከሌላው መሻሉን ያየነው የለም ድርጅታዊ ብቃትና ጥንካሬ ሲያሸቆለቁል እንጂ ሢያድግ አላየንም;; እስከ ዛሬ የተፈጠሩት ሕብረቶችና አንድነቶች ሁሉ የተበተታተኑበት ዋናው ምክንያት የመሪዎች የወንበር ወይም የመሪነት ስግብግበነትና የሚነድፉት የትግል ፕሮግራምና የትግል ስልት መሪዎቹን መልሶ የሚታገላቸው መሆኑ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብም ከእንግዲህ ለጥቃቅን ቡድኖች ወይም ከስም በቀር በትግሉ የማያውቃቸውን ድርጅት ነን ባዮች ሁሉ ከመድረኩ ማስለቀቅ ይጠበቅበታል ;; በዲሞክራሲ ስም ትግሉን የሚያዳክሙ ድርጅቶችን በቁርጠኝነት ወያኔን የሚታገለውን ያህል ሊታገላቸው ይገባል;; ትግሉ ወደድርጅቶች ጥራት መሸጋገር ይኖርበታል;; በራሱ ችግር ያኮረፈ ሁሉ በህዝብ ስም በብጥስጥስ ትግል የህዝቡን መስዋእትነት ከንቱ የሚያደርግበት ሁኔታ መወገድ ይኖርበታል።

## 2/ በራስ ተማምኖ ከድክመት አገግሞ መነሳት የጠንካራ መሪ ባህሪይ ነው

በትግል ሂደት የሚታዩ የተስፋ መቁረጥ አዝማሚያዎች ሊኖሩ መቻላቸው የፖለቲካ ሕይወት አንዱ ባሕርይ መሆኑ ግንዛቤ ተገኝቶበት ከዚህ ተስፋ መቁረጥ ስሜት ተላቀው በራስ የመተማመን እና በአሸናፊነት ስነልቦና ከስህተት በመማር በአዲስ መንፈስ ትግሉን ማጠናከር ነው:: ባለፉት አመታት በትግል አለም ገብተው ስማቸው በመጥፎ ሳይነሳ ወይም መጥፎ ቀለም ሳይቀባ ያሉ የቆዩ ማንም መሪ አልታየም ወደፊትም አይታይም:: የሚፈለገው ግን ከስህተቱ ለመማር የተዘጋጀ ከራሱ ጥቅም ለህዝብ ጥቅም የቆመ በራሱ የመተማመን ያለውና ሕዝባዊ ፍቅር ያለው መሪ ነው:: ነገር ግን አለማደግ ሆኖ አላደግንም የጥላቻ ፓለቲካ እንጂ የመፍትሄ ፖለቲካ መሪዎች አላፈራንም;;ትንሽ የህዝብ ድጋፍ ሲገናጸፉ ወደ ንጉሳዊነት መቀየር የሚሹ እንጂ በአላማቸው ጸንተው የሚቆዩ መሪዎች አልፈጠርንም ;; ከሚፈጥር አዕምሮ ይልቅ ብሩህ አዕምሮ የሚገድል የሞተ አዕምሮ ተሸካሚዎችመም በሀህበብረተሰበባቸችነንነን መሞለልተቶአለል :: ይህን ግንዛቤ በማስገባት አሁንም በየትኛውም ድርጅት የተሰለፈ ለዚያች ሀገር የቆመ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ጠላት ሳይሆን ከስህተት እንዲመለስ የሰላማዊ ትግሉ እምብርት መሆን የሚኖርበት::

**3ኛ. አሁንም ብሔራዊ እርቅ አማራጭ የሌለው የሰላማዊ መንገድ ነው**:: አቶ መለስና ተከታዮቻቸው ስለብሔራዊ እርቅ ሲነሳ ምንና ማን ተጣላ ብለው እንደሚያሾፉ ባለፉት የትግል አመታት የሰጡት ምላሽ ያይቷል:: ለብሄራዊ እርቅ ብለው የሚጮሁት ተቃዋሚ ሃይሎችም ሆኑ መንግስት ስለብሔራዊ እርቅ ተገቢው ግንዛቤ ለማግኘታቸው ግን እርግጠኛ አይደለሁም:: አልያም እኔ የምገምተው ብሔራዊ እርቅ የተለየ ሊሆን ይችላል:: በበኩሌ ብሔራዊ እርቅን አቶ መለስና አቶ ሃይሉ ሻውል ዶ/ር መራራ ወይም ዶ/ር በየነ ወይም አቶ ኢብሳ ዳውድ እጅ ለእጅ ሲጨባበጡና ፎቶግራፍ አብረው ሲነሱ ማየት አይደለም::

ብሔራዊ እርቅ የመሪዎች መጨባበጥ ስይሆን የሕዝብ ልብና አዕምሮ መለወጥ ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ከላይ ብቻ የሚመጣ ሳይሆን ከታች የሚመነጭ ነው:: እዚህ ላይ እንደብዙ ጸሀፊዎች ከዚህ አገር ወይም ከዚያ አገር ልምድ እየጠቃቀስኩ ማቅረብን ብዙ አልመርጠውም አንዱም የችግራችን መንስኤ ከየቦታው የምንቃርመውን አስተሳሰብ ከነባራዊ ሁኔታችን ጋር ስለማይመጣጠን ነው:: በበኩሌ በኢትዮጵያ ብሔራዊ እርቅ መጀምር ያለበት በቅድሚያ ለሕዝብ ቁመናል ከዚህ መንግስት እንሻላለን በሚሉ ድርጅቶች መሆን አለበት:: ቅንጅትና ሕብረት የጎጥ እየተያየ ስለ ብሔራዊ እርቅ ኢህአዴግን መጨቃጨቅ ትርጉም የለውም:: ሕብረት ውስጥ የታቀፈው ፖለቲካ ድርጅት እርስ በርሱ እየተጎነታተለ ስለብሔራዊ እርቅ ማውራት የሞራል ብቃት ሊኖር አይችልም::

ብሄራዊ እርቅ ከዚያም አልፎ የግለሰብን አመለካከት ፍጹም መለውጥ ይጠይቃ ጽኑ እምነት ይጠይቃል አንዱ ከሌላው እበልጣለሁ በሚል መንፈስ ተኮፍሶ ብሔራዊ ሰላምን ሊያመጣ አይችልም:: ለእነ አቶ መለስ ይህ ዛሬ ትርጉም የለውም ምክንያቱም ኢኮኖሚውም ሆነ ጠመንጃው ከአመራራቸው አልወጣም:: ያልተረዱት ነገር ቢኖር እየተለወጠ የሚሄድ መሆኑን ነው:: ይህ ከደርግ አልተማሩም ወይም ደርግን አሸንፈው የገቡት በወቅቱ የነበረው ሰራዊት ለመዋጋት ፍላጎት አለመኖር የጥቂቶቹን የበላይነት ወይም አጉል አመራር የፈጠረው ቀውስ ውጤት መሆኑን በሚገባ ካለማጤንና ጊዜ

የሚፈፐረውን ጀግንነት ጊዜ እንደሚለውጠው አለተረዱም:: አሁንም ብሔራዊ እርቅን በሰላማዊ ትግሉ እምብርት አድርጎ ሊንቀሳቀስበት የሚገባበት ዋናው ምክንያት የራስንም ሆነ ድርጅታዊ ህልውናን ለማስጠበቅ ስለሚያስችል ነው:; በሀገራችን ያልተለመደ በመሆኑ ለዚህ አይነት ሁኔታ የሕዝቡን አመለካከት ማጎልበት ይጠበቃል::

## 4/ ጽንፈኝነትን አጥብቀን ልንዋጋው ይገባል

አንዳንድ ወገኖቻችን ኢህአዴግን ሲኮንኑት በተለይም መሪ የሆኑትን አቶ መለስን አንዳንዴ ከነሂትለር ከነ ሞሶሎኒ ጋር ለማወዳደር እየቃጣቸው የከረረ ጥላቻን ሲያንጸባርቁ ይታያሉ:: በሌላ በኩል የድርጅት መሪዎችንም የተለያዩ ቅጽሎችን እየሰጡ ሲያብጠለጥሉዋቸው እናያለን;; በዘሁ አንደበታችን ሰለሰላማዊ ትግል ደግሞ እንናገራለን ;; ሁለቱ የማይጣጣምና የሚጋጭ ነው: ይህ ደግሞ የቃርሞ ፖለቲካ ውጤት ነው:: ስለሰላማዊ ትግል ሲነሳ ጋንዲን ስለጭካኔ ሲነሳ ሂትለርን ካልጠቀስን አስተምሮአችን የተሳካ አይመስለንም:: በራስ ካለመተማመን የሚመነጩ ችግሮች ናቸው::

አቶ መለስም አንዴ ተቀናቃኞቻቸውን ለመምታት ቦናፓርቲዝም ሌላ ጊዜ ደግሞ ኢንተርም ሃዌ ወ.ዘ.ተ ...የሚል ሀሳብ ይዘው እንደተነሱት ማለት ነው:: እውነታው ግን አለምም አገራችንም ያለችበት ሁኔታ ፈጽሞ የተራራቀ ነው:: እንደ ጋንዲ በሰንደል ጫማ ሕዝብ መሀል ተጉዞ ተርቦ ስለሰላም የሚሰብክ መሪ በዚህ ወቅት ልናፈራ አንችልም:: የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችንም ስንወዳቸው እንደማንዴላ ሳንፈልጋቸው ደግሞ የአስቀያሚ መረዎችን ቀለም እየቀባን ያልሆኑትን እንዲሆኑ የማድረጉ ሰብእናን መካብ ወይም መናድ ሊገታ ይገባል;; መሪዎችም እንደኛው ሊሳሳቱ ይችላሉ:: በአመራር ችግርም የሰውም ሆነ ንብረት ውድመት ይከሰታል:: ይህን ድክመታቸውን ማጋለጥ ተገቢ ነው:: አቶ መለስ ዛሬ በስልጣን ላይ ስላሉ ከሂትለር ከሙሶሎኒ ጋር እያወዳደርናቸው እውነተኛ ማንነታቸውን እንዳንነዘብ አድርጎአል;; ከሂትለርና ከሙሶሎኒ ጋር ተቀምጦ ስለሰላማዊ ትግል ማውራት ይቻል እንደነበረ አላውቅም:: ይልቁንም ወደዚያ እንዳይሸጋገሩ ድርሻችንን ማበርከት አለብን ;; እንኳንስ ብዙ ሰራዊት ከሁዋላዬ አለ ብሎ የሚያስብ ይቅርና አጠፋሀለሁ ሲባል ቆሞ የሚጠብቅ ተራ ግለሰብም አይኖርም:: ወይ ይሸሻል ወይ አስቀድሞ ይገድላል:: ኢየሱስ ብቻ ነው እንደሚገሉት እያወቀ ሌላውን ለማዳን ራሱን አሳልፎ የሰጠው::

አንድ የመንግስት መሪ የሚመዘነው ካለው አገራዊ ሃላፊነት የአመራር ደረጃ ነው:: የዲሞክራሲው አባት የሚባለው አሜሪካን መሪ ቡሽ በተሳሳተ አመራራቸው በኢራቅ ያለቀው ኢራቃዊም ሆነ አሜሪካዊ ቁጥርና ድርጊቱም የሚዘገንን ነው;; ሕዝባቸው ግን ከሂትለር ጋር አልመደባቸውም ተቀናቃኞቻቸውም በዚያ መልክ አልፈረጁዋቸውም ። የተሳሳተውን አመራር ውጤት በተስተካከለ አመራር ለመለወጥ የሚደረገውን ትግልም እያየነው ነው:: ልዩነቱ ለአቶ መለስ ስህተተኛ መባል ሞት ነው;; ምክንያቱም የእሳቸው ቃል እንደእግዚአብሄር ቃል እንዲታመንበት የሚሹ መሆናቸው ነው። ልዩነቱ ቡሽ ተከብረው ወደቴክሳስ መኖሪያቸው ሲጓዙ አቶ መለስ ለስደት የሚያበቃ ዝግጅት ላይ የሚቆዩ መሆናቸው ነው:: ይህ እሳቸው የፈጠሩት ብቻ አይደለም እኛም እየፈጠርንባቸው ያለ ፍርሃት ነው:: አሜሪካንን የጠቀስኩት በውጭ የሚገኙ አንዳንድ ወገኖቻችን አስተያየቶች የሚያስፈራና ስለሌላ አለም የሚናገሩ እንጅ ስለኢትዮጵየ ስለማይመስለኝ ነው። ስለሚዘገነንንም ጭምር ነው። እንግዲህ ብሔራዊ እርቅ እንዲህ አይነቱ አዝማሚያ እንዲጠፋ ነው ሁሉም መረባረብ ያለበት::

ቅንጅትም ሆነ በሕብረት የተፈጠረው መበታተን የበጀው ለኢህአዴግ በስልጣን መቆየት ነው:: ኢህአዴግ አምባገነን ብቻ ሳይሆን ብልጥ ድርጅትም በመሆኑ የሁሉንም በሽታ እያዳመጠ የራሱን ህልውና ሊነኩ የማይችሉ የተቃዋሚ ጥያቄዎችን በተዘዋዋሪ መንገድ መልስ እየሰጠ የውጤት ባለቤት ሆኖ ለመታየት ብዙ ጥረት አድርጓል እያደረገም ነው:: ለዚህም በሀገራችን ለውጥ አለ እንቅስቃሴ አለ:; ሰላማዊ ትግሉ አልሞተም ቅንጅት ወይም ህብረት ስልጣን አልጨበጡም ;; ነገር ግን ትግላቸው ፍሬ አላጣም:: ቅንጅት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ድርጅቶች መንፈስ አለላቸው ;; የተሳሳተ የድርጅት መንፈስም ትክክለኛ መንፈስም አለ የተሳሳተው እየተንጠባጠበ ትክክለኛው መንፈስ እያበበ ይሄዳል:; የተሳሳተው መንፈስ ተስፋ ቆርጦ በአደገኛ መስመር ሲጓዝ ትክክለኛው መንፈስ ከድክመቱ ተምሮ ተጠናክሮ የህዝበብ ድምጽና ሃይል ሆኖ በአሸናፊነት

ይወጣል::

## 5 ማጠቃለያ

በመጨረሻም የችግሩ  ሁሉ  ስነልቡናዊ መሰረት  በመንግስትም ሆነ በተቃዋሚዎች ውስጥ ያሉ ጽንፈኞች የበላይነት የኔነት ስሜት ነው:: ብዙ የነቃን የሚመስለን ብዙዎቹ ግን የነቃ አዕምሮ የሚባለው ደረጃ ላይ ያለመድረሳችንን ያመለክታል ;; የነቃ አዕምሮ ራስ ወዳድነትን እኔነትን አሳልፎ የሰጠ አዕምሮ ነው::  የግለሰብ አዕምሮ በዚህ ደረጃ ላይ አለመድረስ ግለሰቡ የተሰባሰበበት ቡድን ላይ ይንጸባርቃል:: ከቡድንም ወደ ድርጅት ከዚህም ከፍ ሲል ቡድኑ መንግስት ሲሆን መንግስት ላይ ይንጸባርቃል:: ከግለሰብ እኔነት የቡድን ወይም የድርጅት የኔነት  ቀጥሎም ወደ መንግስታዊ የኔነት መሸጋገር የሰላም የፍትህ የእኩልነት መሰረታዊ ችግር በመሆኑ በቅድሚያ ግለሰባዊ እኔነትን እንታገለው:: ይሄ ዋናው በሽታችን ነው;; እኔ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢም ከእዚህ ነጻ አለመሁኔን እያወቅኩ እየታገልኩት ነው የጻፍኩት ;; በኢህአዴግም ሆነ በአንዳንድ ተቃዋሚዎች በፍቅር በሰላም ተከባብሮ የኖረውን የሀገራችንን ሕዝብ ልዩነቱን እያሰፋን  በስም ተቃዋሚ በተግባር በአንድ ፈርጅ እየተሰለፍን  ተቃዋሚና ደጋፊ ስም ለጣጥፈን እንዲፋጅ ቀስቅሰን ቀስቅሰን እስካሁን በህዝብ አሸናፊት ከከፋ አደጋ ተርፈናል;; ከማንኛውም አደጋ ለመዳን መፍትሔው ሰላማዊ ትግል ብሔራዊ መግባባት እርቅ ብቻ ነው:: ከሁሉም በላይ ትግሉ ማተኮር ያለበት በብሔር ብሔረሰብ ድርጅቶችና በኅብረ ብሔር ድርጅቶች መካከል ያለውን ልዩነት አጥቦ ኢትዮጲያዊ የትግል ስልትና መፍትሄ  መቀየስ ነው።

አንተ ነፍጠኛ ወያኔ ኢሰፓ ኦነግ ቅንጅት ኢደፓ መኢሶን ኢህዴፓ ኢድዩ ደቡብ ሕዝቦች የጋንቤላ ህዝቦች የአርበኞች ግንባር ሌላም እየተባባልን በመተቻቸት ለዛች አገር የእናትና የእንጀራ ልጅ ሆኖ በመተያየትና በጥይት እየተፈላለጥን ወንድም በወንድም ሬሳ ላይ ነጻነትን ማወጅ ትርጉም የለውም ። ደምን በደም ማጽዳት አይቻልም ትርፉ ደም በደም መሆን ነው;;

እስከ ወያኔ መንግስት ያሳለፍለውንና የተከፈለውን መስዋትነት ሳስበው የተከፈለው ዋጋ ከንቱ ነው ወደሚል እምነት እያጋደለኝ ነው:: የሁላችንም የቀረበ ትዝታ እንደመሆኑ የአንድ ትውልድ ህዝብና ኢኮኖሚ ያላንዳች ጥቅም  ባክኖል። ዛሬም በኢሃዴግና በተቃዋሚዎችም  የቂመኝነትና ግትረኛ አቅዋም የተነሳ  የሚቀጥለውንም ትውልድ ለአበሳ ዳርገነው እንዳናልፍ የተበረዘውን መንፈሰ ማደስ የወቅቱ  የትግል አቅጣጫ  ሊሆን ይገባል። ከ10 አመት በሁዋላ  በቸንቐ እንኩዋን የሚግባባ ትውልድ እንደምናጣ ጉዞአችን  እያሳየን ነው።

Contact address

*shimelisw@yahoo.com*